የ17 ዓመቷ ወጣት **ህሊና ደሳለኝ** ፣ የኢሕአዴግ አዛውንቶችን በጨዋ ደንብ መነገር ያለበትን ሁሉ ተናግራለች ብዬ ስለማስብና ፣ የወጣቷም መልዕክት የመላው ኢትዮጵያዊውን ልባዊ ምኞት ይናገራል ብዬ ስላመንኩ ፣ የወጣቷን ሙሉ ግጥም በፅሁፍ ላቀርብላችሁ ወደድኩ ።

የልጅ አዋቂ ይህን ያክል ጥልቅና ረቂቅ መልዕክት ለተጨፈኑ አዛውንቶች ማስተላለፍ ከቻለች ውሃም ሽቅብ መውረድ ቢጀምር ከማመን ወደኋላ አልልም ።

# የማጀት ስር ፣ ወንጌል

**ሙያተኛ አገሬ ፣ ከማጥገብ ጎደለ ፣ በረከት አራቀው ፣ የገበታሽ ለዛ**

**ተሻምቶ ለመጉረስ ፣ ከበላነው ይልቅ ፣ የደፋነው በዛ ።**

**ሙያሽ ባያስደፍር ፣ አጀብ ቢሰኙበት**

**ማዕዱ ቢሙላላ ፣ አይነቱ ቢያምርበት**

**አበዛዙ አይደለም ፣ አበላሉ ላይ ነው ፣ የገበታሽ ውበት ።**

## እየተማመንን !

**የፋክክር ቅሚያ ፣ በርሃብ እየናጠን**

**ከደፋነው ጠግቦ ፣ ውሻችን በለጠን ።**

**ከምርት አላነስን ፣ ጎተራችን ሙሉ ፣ ጀግና አራሽ ፣ መች አጥተን**

**ማሰብ የጎደለው ፣ አያያዛችን ነው ፣ ገደል የከተተን ።**

## ይልቅ ግድ የለሽም !

**ከምግባር ምጣድ ላይ ፣ ሳንበስል አንጋግተሽ ፣ ከማዕድ አትምሪኝ**

**ገበታሽ እንዲያምር ፣ ከእግዜር የሚያስታርቅ ፣ ፍቅር አስተምሪኝ ።**

## ገበታ ዕድሜ ነው !

**ባለማሰብ መክነን ፣ ሳንፀነስ ጃጅን ፣ ሳንጣድ አረርን**

**ከዘመን ገበታ ፣ ከፊደል አቅድመን ፣ ዘር እየቆጠርን ።**

## ገበታ ሃቅ ነው !

**በክፋት ሊጥ ጋግረው ፣ ያሻገቱት ዕውነት**

**በሆዳም እስክስታ ፣ አረግጠው ያፈኑት ፣ የምስኪናን ጩኸት ።**

## እስኪ ልጠይቅሽ?

**በጥም ደዌ ደቆ ፣ የርሃብ ጠኔ ደፍቶት ፣ ዕልፍ ትውልድ ያልፋል**

**ቢራ ለመጥመቂያ ፣ የሚበተን ገብስ ግን ፣ ካገር መች ይጠፋል ።**

ከሆድ በማይሻገር ፣ የማጀት ቤት ዕውቀት ፣ አጥብበሽ አትለኪኝ

እስኪ መኖር ይግባን ፣ ከማስተዋል መቅደስ ፣ ሰው መሆን ስበኪኝ ።

ዘመን ካልገበረው ፣ ከችጋር ተራራ ፣ ከሲያል ዳር ኑሮ

እንዴት ነው መሻገር ፣ ከመርፌ ቀዳዳ ፣ በጠበበ አይምሮ ።

ከምስኪን ዘመን ላይ ፣ የማይኖሩበትን ፣ ዕድሜ መበዳደር

ላንዲት ማምሻ ደስታ ፣ ባያት እስትንፋስ ላይ ፣ ቁማር መደራደር ።

**ያሳፍራል አይደል?**

እያደጉ ማነስ ፣ እያነሱ መዝቀጥ

አጎንብሶ ያፀናን ፣ የደሃ እናት ጉልበት ፣ በጭካኔ መርገጥ ።

**ያሳፍራል አይደል?**

መንገስ ከሚያባላህ ፣ መንግስት ከሚያቃቅር ፣ ማግኘት ከሚያጎለን

ማጣት ውሎ ይግባ ፣ ባርነት ይሰንብት ፣ ድህነት ይግደለን ።

ከረፈደ ፀፀት ፣ ደረት እየደቁ ፣ ከእግዜር ቢዋቀሱ

ትርጉሙ ምንድነው ፣ ሲኖር ተቃቅሮ ፣ ሲሞት መለቀሱ ።

በናታችን አድባር ፣ በፍቅሯ ይሁንብን

መድመቅ ካጋደለን ፣ ቆሽሸን ይመርብን ።

በመጠማት ሲቃ ፣ እስትንፋስ እስኪያንቃት ፣ ነፍሳችን ትርበትበት

ብቻህን ከመጥገብ ፣ አብሮ መራብህ ነው ፣ ሰው የመሆን ውበት ።

በድፍን ግልብ ፣ እሚያጋድል ፣ ሕዝብ የመሆን ፣ መንጋ አይንዳን

በማሰብ ስር እንፈወስ ፣ በሰውነት ፀበል እንዳን ።

**እየህ ሰው ስትሆን !**

ከመንጋነት የሚያግድ ፣ እረኛ አያሽህም ፣ ከህሊናህ በላይ

ስታስብ መሪ ነህ ፣ በብስለት ከፍታ ፣ በማስተዋል ሰማይ

**እየህ ሰው ስትሆን !**

የጎጥ አረም ነቅለህ ፣ ባንድነት መስክ ላይ ፣ ፍቅር ትዘራለህ

በወረወሩብህ ፣ የጥላቻ ድንጋይ ፣ ትውልድ የሚያፋቅር ፣ ድልድይ ታበጃለህ ።

**እየህ ሰው ስትሆን !**

ዝምታህ ኃያል ነው ፣ ጀግና የሚያንበረክክ ፣ ከፈሪ ቀረርቶ ፣ ከባዶ ሰው ጩኸት
ሐገር ለምስ ከሚል ፣ በመንደር አጀንዳ ፣ ባሸኮለሌ ተረት ።

## አየህ ሰው ስትሆን!

ነፃ ነህ እያሉህ ፣ መታሰር ያምርሃል ፣ መቀመቅ መበስበስ ፣ የኖርክለት እውነት ፣ ሐገር እስኪፈታ
በሃቁ እስኪመዘን ፣ ስለ በርባን ክብር ፣ የቆሸሸው ፍቅር ፣ የታሰረው ጌታ
ከድል ታሪክ ሰማይ ፣ ከስልጣኔ ዳር ፣ ከጥበብ ከፍታ
እንሻገራለን ፣ ሕዝብነትን ትተን ፣ ሰው የሆንን ለታ ።
በትረ ጥበብ ቢካን ፣ ዓለም ሊያንቀጠቅጥ ፣ ድል ስልጣን ቢሰጠው
ጀግና መሪ አይደለም ፣ ብርቱ ተመሪ ነው ፣ ሐገር የሚለውጠው
አስተውል ወዳጄ ፣ ጠልተን ላንጣለ ፣ ችለን ላንጋደል ፣ ነደን ላንፋጀው
የኛው ትርምስ ነው ፣ በልቶ ለሚያባላ ፣ ጠላት የሚበጀው ።
ስጋና ደም እንጂ ፣ ያንድነታችን ውል ፣ የፍቅራችን ቀለም
ያሰመርነው ክልል ፣ የታጠርንበት ዘር ፣ ቋንቋችን አይደለም ።
ከመዋሃድ መቅደስ ፣ ትውልድ እናስተምር ፣ ዘመን ይመርቀን
ፍቅራችን ምን ጎሎት ፣ ደማችን ያስታርቀን ።
በልጆቿ አጥንት ፣ በደም ኪዳን ምለን ፣ የገባንላት ቃል
ከጩኸት ያለፈ ፣ ዘመን የሚሻገር ፣ ተግባር ይጠይቃል ።
ባንድ ሃሳብ ተጋምደን ፣ በድል ፣ ድር እናብር ፣ ውድቀታችን ያንቃን
ሰርተን እናሳምን ፣ ሆነን ድል እንንሳ ፣ ያፍ ጀግንነት ይብቃን ።
ምስኪኒቷ እናቴ ፣ በሞላ ጎዳና ፣ ባልጠበበ ድንበር ፣ በዘር ገመድ ታግዳ
ነፃ ነኝ ትላለች ፣ መንጋነት ያሰረው ፣ ባሪያ ትውልድ ወልዳ ።
የጀግንነት እብሪት ፣ ልባችንን ደፍኖት ፣ ማሰብ እየከዳን
እንዴት ነው ነፃነት ፣ እንዳበደ ፈረስ ፣ ስሜት እየነዳን ።
ገሎ የመንገስ ጥማት ፣ ጩኸት ላገነነ ፣ አመፅ ላጀገነው
ለዚህ ምስኪን ትውልድ ፣ በጅምላ እየነዱት ፣ በመንጋ እያሰበ ፣ ነፃነት እንዴት ነው?
ነፃነት ምርጫ ነው ፣ አምሮ ቢደላደል ፣ ጥፋት ያመነነው ፣ የመንጋዎች መንገድ
እንቅፋቱ ወዶ ፣ ለኖሩለት እውነት ፣ ለብቻ መራመድ ።
ነፃነት ማመን ነው ፣ ቀን ወዶ ቢያጀግን ፣ ቀን ጠልቶ ቢከዳም

ቢቆሸሹም ቢደምቁም ፣ እራስን መቀበል ፣ እራስን መምሰል ነው ፣ የነፃነት ገዳም ።
ነፃነት ማሰብ ነው ፣ ባንድነት መለምለም ፣ የኔነትን አረም ፣ ከህሊና ማጥፋት
ዘር ሆኖ ከማለፍ ፣ ሐገር ሆኖ ማበብ ፣ ዓለም ሆኖ ፣ መስፋት
ንገረት ላገሬ ፣ በጀግኖቿ ትግል ፣ ድንበር ባታስደፍር ፣ ከጅ ገዥ ብትወጣ
ነፃ ነኝ እንዳትል ፣ በገዛ ልጆቿ ፣ በጅ አዙር ተሸጣ ።
ስሩን ካልሸመነው ፣ በመዋሃድ ጥለት ፣ በማስተዋል ሸማ
ታሪክ አናደምቅም ፣ በጭብጨባ ድግስ ፣ በሆይሆይታ ዜማ ።
ምን ብናቀነቅን ፣ በየሰልፉ ሜዳ ፣ ወኔ ብንደግስም
በፈረሰ ዓይምሮ ፣ በደቀቀ አንድነት ፣ ሐገር አናድስም ።
በጭፍን ከመሮጥ ፣ አስቦ ማዝገም ነው ፣ የመራመድ ውሉ
ሁሉም እንቅፋቶች ፣ እስኪጥሉን ድረስ ፣ ምርኩዝ ይመስላሉ ።
በድፍን ግልብ ፣ እሚያጋድል ፣ ሕዝብ የመሆን መንጋ ፣ አይንዳን
በማሰብ ስር እንፈወስ ፣ በሰውነት ፀበል እንዳን ።
ከእግዜር ልንወዳጅ ፣ ለምህረቱ ጥላ ፣ ዕምባ ብንደግስም
ልብን ሳይመልሱ ፣ ለንሰሃ መሮጥ ፣ ከፅድቅ አያደርስም ።
ውብ ነገን እናውርስ ፣ ትላንትን አክመን ፣ በይቅርታ ፀበል
ትውልድ ይጨርሳል ፣ ያረገዝነው ዕንባ ፣ የቋጠርነው በቀል ።
ከመስጠት አንጉደል ፣ ከቀማኞች ገደል ፣ ተረግጠን ብንጣል
ካሸከሙን በቀል ፣ የምናወርሰው ፍቅር ፣ ሐገር ይለውጣል ።
ከድሏ ጣሪያ ላይ ፣ ዘር የቀዳደደው ፣ ሸንቁሮ ቢበዛም
ያ ከንቱ ፎካሪ ፣ ባፈጀ ቀረርቶ ፣ ሺ ጉራ ቢነዛም
ሚሊዮን ዘር ቢሸጥ ፣ አንድ ሐገር አይገዛም ።
ኢትዮጵያዊነት ነው ፣ የትርታችን ልክ ፣ የነፍሳችን ግጥም
መልስ ቤት በራቀው ፣ በከረመ ፀሎት ፣ ሰርክ ብታንጋጥም
አጎንብሳ ደሃ ፣ ባፀናችው ጉልበት ብትረጋገጥም
ነፍሷን አደህይታ ፣ ባሸረችው ቁስል ብትገሸለጥም
ሐገር ሆና ገዝፋ ፣ በየ ጎጣ ጎጡ ፣ አትርመጠመጥም ።
የዘመን ዕውነት ነን ፣ ከደግነት ሰማይ ፣ በጥበብ የኖርን

ትዕግስትም ልክ አለው ፣ ፈርተን እንዳይመስለው ፣ ስላቀረቀርን ።

ማተብ አስሮን እንጂ ፣ ተጣልተን እንዳንቀር ፣ በክፍፍል ገደል

ካገር ክብር በልጦ ፣ ሞት ብርቃችን አይደል ።

ንገሩት ለዚያ ሰው ፣ ከዓለም ጫፍ ፣ እስከ ጫፍ ፣ ኃይል እንደ ተራራ ገዝፎ ቢከመርም

ክንዱን አፈርጥሞ ፣ እልፍ የሰገደለት ፣ ጀግና ቢሰድርም

ዓለም የሞተበት ፣ የጠላት ማርከሻ ፣ ጦር ቢደረድርም

ባአንድ አይናችን ሰላም ፣ በኢትዮጵያችን ክብር ፣ አንደራደርም ።






https://www.youtube.com/watch?v=Z0XMqhbemsM

ገጣሚ ህሊና ደሳለኝን ለማድመጥ

ማስፈንጠሪያው ላይ ይጫኑ

ነገርኩህ ብትሰማ ፣ ደግሜ ደግሜ

እጭንጫ ላይ መዝራት ፣ ካልሆነ ድካሜ !

አለችው እንበል ይሆን? (ታዛቢው)

September 13, 2019